# ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት፡፡
# Ethiopia: The Kingdom of God Services

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፥ ኢትዮጵያውያንም፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኾናቸውን ለማስረዳት፥ የ“ኢትዮጵያ” እና “የኢትዮጵያውያን” የኾነውንም ኹሉ ለመጠበቅና ለማሳወቅ፡፡
To reveal the truth about Ethiopia's entity as the Kingdom of God and Ethiopians' identity as the People of the Holy Covenant with God; and so, to safeguard and promote all that pertains to Ethiopia and Ethiopians.

ሓምሌ ፳፯ ቀን፥ ፳፻፫ ዓ. ም.

ይድረስ ለአቶ ዳዊት ብርሃኑ፤

ባሉበት።

በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና በቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ስም፡ ኢትዮጵያዊ ሰላምታዬን አቀርብልዎታለሁ።

በፈረንጆቹ አቆጣጠር፡ በ8/3/2011 የተላለፈው እ-ጦማርዎና በዚያው፡ በባዕዳኑ አቆጣጠር ብቻ ሳይኾን፡ በአኀዛቸው ጭምር፡ *01.08.11* ብለው ጽፈው፡ ከእርሱ ጋር፡ በዐባሪነት የላኩልኝ ማስታወሻ ደርሰውኛል፤ እግዜር ይስጥልኝ!

*"ለቀጣዩ ዓቤቱታዬ ፈጣን መልስ ባገኝ ምኞቴና ጸሎቴ ነው።"* ስላሉ፥ ራስዎንም፡ "ጊዜ ያልፈጠረልኝ፡ ብኩን ግለሰብ ነኝ!" በማለት፡ ማንነትዎን፡ በራስዎ አገላለጽ ስላሳወቁ፡ ከዚህ የተነሣ፡ እርስዎም፥ እኔም፡ በማያስፈልግ የጽሑፍ ልውውጥ፡ ዕንቍ ጊዜያችንን፡ በከንቱ ልናባክን ስለማይገባን፡ ይኸው፡ ፈጣኑን ምላሼን፡ እንዲህ በሚል፡ አጭር ቃል ልኬልዎታለሁ።

እኔ፡ አኹን፡ መልስ እንድሰጥባቸው ያቀረቡልኝን ጥያቄዎችና እንድተችባቸው የዘረዘሩልኝን ነገሮች ኹሉ በሚመለከት፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን መሠረታዊ አቋም አኳያ፡ ሰፊ ትንተናና ሙሉ ሓተታ የሰጠሁባቸው መዛግብት አሉ፤ እነዚህም፡ ባለፈው መልሴ እንዳሳሰብሁዎ፡ አድራሻው፡ www.ekogs.org ወይም www.ethkogserv.org በኾነው የአገልግሎታችን ኀዋ ሰሌዳ ላይ፡ "መጻሕፍት" በሚለው ክፍል ውስጥ፡ ስማቸውና ሥዕላቸው ተለጥፎ በተደረደሩት ዕትሞች፥ እንዲሁም፡ በተለይ፡ "ጥያቄና መልስ"፥ "መልእክቶች"፥ "ደብዳቤዎች" እና "ሃይማኖት" በተባሉት የተለያዩ መድረኮች ውስጥ ተካትተው ይገኛሉ። ስለዚህ፡ እነዚያን በማንበብ፡ የበለጠ እንዲረኩ እጋብዝዎታለሁ።

የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ፡
ንቡረ-እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ።

መልእ. ሣ. ቁ. ፰፻፲፪፤ ስልክና ዕምነቅ ቁ. 0፲፩-፬-፲፮-፲፰-፹፭ እና 0፲፩-፫-፳-00-፹፭፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ፡፡
P. O. Box 812, Addis Abeba, Ethiopia. Tel. & Fax. Nos. 011-4-16-18-85 & 011-3-20-00-85.
P.O.Box 43262, Washington, DC 20010-9262 U.S.A.
Tel. (301) 587-8074 ~ Fax: 301-587-1971 ~ E-mail: info@ethkogserv.org
Website: www.ethkogserv.org